የሰ/መ/ቁ. 109392

ቀን 28/7/2008 ዓ.ም

ዳኞች፡-ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

ፈይሳ ወርቁ

አመልካች፡- አቶ ሶፎኒያስ ሀብተማርያም ጠበቃ ሀ/ማርያም መልካ

ተጠሪ፡- ካልዲስ ኮፊ ኃላ/የተ/የግ/ማ- ጠበቃ አሰፋ መኮንን - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ የሰበር አቤቱታ መዝገብ ክርክር አመልካች አቶ ሶፌኒያስ ሀብተማሪያም ጥር 9/2007 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 104228 ጥቅምት 2/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የቀረበ ሲሆን የአሁን አመልካች የዋስትና ስምምነት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ቢኒያም አሰፋ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በእስቶር ኪፐር ወይም ዕቃ ግምጃ ቤት ሰራተኛ የሥራ ቅጥር መደብ ተመድቦ ሲሰራ ለሚደርሰው የንብረት ጉድለት ዋስ መሆኔ እየታወቀ 1ኛ ተከሳሽ የገንዘብ ያዥነት ስራ እንዲያከናውን ከተመደበበት ስራ ውጪ ከ100000 ብር በላይ በመስጠት በተላላኪነት ተጠሪ እራሱ አሰማርቶት በደረሰው የገንዘብ ጉድለት አመልካች ተጠያቂ ነው ተብሎ መወሰኑ አለአግባብ በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ካልዲስ ኮፊ የኃ/የተ/የግ/ማ በፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ በከሳሽ ድርጅት በቦሌ ቅርንጫፍ ለንብረት ክፍል ሲቀጠሩ 2ኛ ተከሳሽ አቶ ሶፌኒያስ ሀብተማሪያም እስከ ብር 50000 የዋስትና ግዴታ ነሐሴ 8/2004 ዓ.ም በተጻፈ የዋስትና ግዴታ ውል ገብቷል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ በንብረት ክፍል ተቀጥረው በሚሰሩበት ጊዜ መስከረም 2/2005 ዓ.ም ወደ ባንክ እንዲያስገባ ከሳሽ የሰጠውን ብር 111552 ይዘው በመሰወራቸው 2ኛ ተከሳሽ በተገኙበት የንብረት ቆጠራ ተደርጎ የብር 5643.49

ንብረት ጎሏል፡፡ ተከሳሽ በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ሆነው የ1 ዓመት ከ7 ወር ቅጣት ተወስኖባቸዋል፡፡ ስለዚህ 1ኛ ተከሳሽ እና 2ኛ ተከሳሽ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1995 መሰረት በገቡት የዋስትና ውል ግዴታ ብር 117195.49 ከህዳር 2/2005 ዓ.ም በሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ ሲል ከሷል፡፡ የተከሳሾች መልስ የ1ኛ ተከሳሽ መልስ የስራ ኃላፊነቴ የንብረት ክፍል ተቆጣጣሪ እንጂ ገንዘብ የማንቀሳቀስ ኃላፊነት የለብኝም፡፡ ስለዚህ ለብር 111552 በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1) መሰረት ተጠያቂ ልሆን አይገባም፡፡ የብር 5643.49 የንብረት ጉድለት ለተባለው ተጠያቂ ነኝ ሲል 2ኛ ተከሳሽም በሰጠው መልስ የብር 5643.49 ንብረት ጉድለት ለተባለው ብቻ በገባሁት የዋስትና ውል ግዴታ መሰረት ተጠያቂ እሆናለሁ፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ከተቀጠረበት ስራ ውጪ አሰማርተውት ለደረሰው ጥፋት ሀላፊነት የለብኝም ብለዋል፡፡

የፌ.የመ.ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 07408 ግንቦት 27/2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ ብር 111552 በሰነድ ተረክበው ለባንክ ገቢ ያላደረጉና የብር 5643.49 ንብረት ያጎደሉ መሆኑን በቀረበው የሰነድ ማስረጃና 1ኛ ተከሳሽም በጽሁፍና በቃል ክርክር ያመኑ በመሆኑ ተጠያቂ ናቸው፡፡ 2ኛ ተከሳሽ የዋስትና ግዴታቸው 1ኛ ተከሳሽ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው ሲቀጠሩ ለንብረት ጉድለት ኃላፊነት እንጂ ከጥሬ ገንዘብ ብር ጋር በተገናኘ እንዳልሆነ የቀረበው የዋስትና ግዴታ ውል ያስረዳል፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተከሳሽ ለብር 5643.49 ንብረት ለጎደለው ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1933(1) እና 1897 መሰረት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ነው 1ኛ ተከሳሽ ለብር 111552 ከህዳር 2/2005 ዓ.ም ጀምሮ በሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈለው፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ ለብር 5643.49 ከግንቦት 27/2005 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጨምሮ ለከሳሽ ይክፈሉት ሲል ወስኗል፡፡ ለፌ.ከፍ/ፍ/ቤት ከሳሽ ይግባኝ አቅርቦ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 140236 አከራክሮ ሰኔ 16/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለደረሰው የንብረት መጉደል ብቻ ሳይሆን ለገንዘብ መጥፋትና የንብረት መጉደል 2ኛ ተከሳሽ (የአሁን መልስ ሰጪ) በገቡት የዋስትና ግዴታ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤት የመልስ ሰጪን (2ኛ ተከሳሽን) የዋስትና ግዴታ ወሰን በግልጽ ከተጻፈው የግዴታ ዝርዝር አንጻር ተመልክቶ መወሰን ሲገባው 1ኛ ተከሳሽ የስራ መደብ ባልተቀየረበት እና የዋስትና ውሉን ከሰራተኛው የስራ መደብ ብቻ በማያያዝ አለአግባብ መተርጎሙ የዋስትናውን ግዴታ ወሰን አላማ ያላገናዘበ በመሆኑ የደረሰበት የውሳኔ መደምደሚያ ስህተት ያለበት ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አሻሽሎ 2ኛ ተከሳሽ (መልስ ሰጪ) 1ኛ ተከሳሽ ብር 111552 ለጎደለው እና በስር ፍ/ቤት የተወሰነውን ብር 5643.49 ጨምሮ እስከ ብር 50000 ብቻ ተጠያቂ ነው ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች (2ኛ ተከሳሽ) ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 104228 ጥቅምት

24/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ የተባለበት ውሳኔ ጉድለት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ቀርበዋል፡፡ መዝገቡ ተመርምሮ አመልካች ዋስ የሆነለት አቶ ቢኒያም አሰፋ ሲቀጠር በዋስትና ውሉ ላይ የንብረት ክፍል ሰራተኛ መሆኑ በተገለጸበት ከስራ መደቡ ውጪ ባንክ እንዲያስገባ በተጠሪ የተሰጠውን ገንዘብ ይዞ በመጥፋቱ አመልካች ሃላፊነት አለበት ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 28/2007 ዓ.ም በተጻፈ መልስ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል ነሐሴ 8/2004 ዓ.ም በተደረገው የዋስትና ውል የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ በተጠሪ ድርጅት ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለሚያደርሱት የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል እስከ ብር 50000 በጋራ እና በተናጥል የዋስትና ግዴታ ውል ገብተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ቅር የሚያሰኝ ባለመሆኑ ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን አጠንክረው ተከራክረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መዝገቡን እንደመረመርነው የአሁን አመልካች (የስር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ) አጥብቀው የሚከራከሩት የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ በተጠሪ ድርጅት ሲቀጠሩ የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው ሲሆን የዋስትና ግዴታዬም የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ በንብረት ክፍል ሰራተኛነት ለሚያጎድሉት ንብረት እና ገንዘብ እንጂ ከተቀጠሩበት ስራ ውጪ እንዲሰራ ተደርጎ ለደረሰው ጉድለት ሃላፊነት ሊኖርብኝ አይገባም በሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ አቶ ቢኒያም አሰፋ አጉድለዋል የተባለውን በአጠቃላይ ብር 117193.49 ያጎደሉት የስራ መደባቸው ሳይቀየር የንብረት ክፍል ሰራተኛ ሆነው እየሰሩ በነበሩበት ወቅት ነው፡፡ የአመልካች የዋስትና ውል ግዴታ ሰራተኛው ተቀጥረው በሚያገለግሉበት ወቅት ለሚደርሰው የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል ተጠያቂ ለመሆን ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የገቡት የዋስትና ግዴታ ሰራተኛው በስራቸው ወቅት ለሚያደርሱት የገንዘብና የንብረት መጥፋትና መጉደል እንጂ ለሚከራከሩበት የንብረት መጉደል ብቻ ተብሎ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ ያጎደሉትን ገንዘብ የድርጅቱ ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በእጃቸው የገባ ገንዘብ መጉደሉ አመልካች ከገቡት የዋስትና ግዴታ ውል ውጪ የሚባል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት አመልካችን በገቡት የዋስትና ግዴታ ውል መሰረት ሃላፊነት አለባቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 104228 ጥቅምት 24/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 140236 ሰኔ 16/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ ወጪና ኪሳራ ተቻቻሉ ብለናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ ሐምሌ 29/2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው እግድ ተነስቷል ይፃፍ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ቅጂ የስር ፍ/ቤቶች እንዲያውቁት ይድረሳቸው፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ